# የትርፍ ስዓት ክፍያ ወይም የማካካሻ እረፍት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 105/2014

Overtime Pay or Compensatory Leave Implementation Directive No. 105/2014

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
Addis Media Network

ጥር 18፥ 2015

## መግቢያ

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትና ከግብ ለማድረስ እንዲሁም ሚዲያው ከሌሎች የሚዲያ ተቋማት ጋር በስርጭቱና በሽፋኑ እንዲሁም በጥራት የተሻለና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የኤሌክትሮኒክስ የሚዲያ አግባቦችን 24 ሰዓት በመጠቀም ለመረጃ ፈላጊው ማህረሰቡ ወቅታዊ ታማኝና ጥራት ያላቸውን መረጃዎችን ተደራሽ እያደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ሚዲያው 24 ሰዓት እያሰራጨ እንደመሆኑ መጠን ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ ገብተው ለሚሰሩ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ወይም የማካካሻ እረፍት ማስፈጸሚያ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1

### ስያሜ

ይህ መመሪያ "አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ የማካካሻ እረፍት የሰራተኞች ማትጊያ መመሪያ ቁጥር 105/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

2.1. **"ተቋም"፡-** ማለት አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ማለት ነው

2.2. **"አዋጅ"፡-** ማለት የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ማለት ነው

2.3. **"ቦርድ"፡-** ማለት አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በበላይነት የሚመራ የስራ አመራር ቦርድ ነው፡፡

2.4. **"ዋና ስራ አስፈጻሚ"፡-** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈጻሚ ነው፡፡

2.5. **"መደበኛ የሥራ ሰዓት"፡-** ማለት ሰራተኛው የመንግስት የሥራ ሰዓት ወይም በሺፍት ገብቶ የሚሰራበት የሥራ ሰአት ነው፡፡

2.6. **"የትርፍ ስዓት"**፡- ማለት ሰራተኛው ከመደበኛ የስራ ስዓት ውጭ የሚሰራው ስራ ነው፡፡

2.7. **"የትርፍ ስዓት ክፍያ"**፡- ማለት ከመደበኛ የስራ ስዓት ውጭ ገብተው ለሚሰሩ ሰራተኞች የሚከፈል ክፍያ ማለት ነው፡፡

2.8. **"የትርፍ ስዓት ማካካሻ እረፍት"**፡- ማለት ከመደበኛ የስራ ስዓት ውጭገብተው ለሚሰሩ ሰራተኞች የሚሰጥ የማካካሻ ዕረፍት ማለት ነው፡፡

2.9. **"ደንብ"**፡-የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የሰራተኞች አስተዳዳር ደንብ ቁጥር 5/2012 ነው፡፡

2.10. **ሰው** ፡-ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## አንቀጽ 3

## የመመሪያው ዓላማ

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የያዘውን ራዕይና ተልዕኮ ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ከመደበኛ የስራ ስዓት ውጭ ገብተው ለሚሰሩና ውጤታማ ለሆኑ ሰራተኞች የሚከፈል የትርፍ ስዓት ክፍያ ወይም ማካካሻ ዕረፍት ለመስጠት ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 4

## ስለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ወይም ማካካሻ እረፍት

### 4.1. የትርፍ ሰዓት ወይም የማካካሻ እረፍት የሚያስፈልጋቸው የስራ ክፍሎች

ሀ/ በትርፍ ስርዓት ክፍያ ውስጥ የመጀመሪያው አማራጭ የሚሆነው ስራውን በማይጎዳ መልኩ የደይ ኦፍ ማካካሻ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

ለ/ በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች በትርፍ ሰዓታቸው ገብተው መስራት እንዳለባቸው የተቋሙ ምክትል ስራ አስፈጻሚዎችና በዳይሬክተሩ ወይም በተወከለው አካል

ሲታመንበት እንደስፈላጊነቱ ገብተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በትርፍ ሰዓት ገብተው ለሚሰሩ ሰራተኞች ትርፍ ሰዓት ክፍያ ቀመር መሰረት የሚከፈል ሲሆን ትክክለኛነቱን በዳይሬክተሩና በምክትል ስራ አስፈጻሚዎች ወይም በዲቪዥን ሃላፊዎች ሲረጋገጥ ብቻ ክፍያ ይፈፀማል፡፡

## 4.2. የትርፍ ሰዓት ስራ እንዲሰራ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች

የተቋሙ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ስራ እንዲሰራ የሚደረገው ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተቋሙ የትርፍ ሰዓት ስራ ማሰራት ይችላል፡፡

## 4.3. የትርፍ ሰዓት ስራ እንዲሰሩ የማይገደዱ

እድሜያቸው ከ14 እስከ 18 አመት የሚሆኑና ለህፃናት ፕሮግራም አስተዋዋቂነት የሚቀጠሩ ታዳጊና ወጣት ሰራተኞች ከዚህ በታች ባሉት ሰዓቶችና ቀናት እንዲሰሩ አይገደዱም፡-

ሀ/ ከምሽቱ 4 ሰአት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት

ለ/ በህዝብና በሃይማኖታዊ በዓላት ቀናት ማሰራት የተከለከለ ነው

## 4.4. የትርፍ ሰዓት ስራ ክፍያ አከፋፈል

4.4.1. የትርፍ ሰዓት ስራ የሚሰራ ሰራተኛ ቢያንስ ከመደበኛ ደመወዙ በተጨማሪ ቀጥሎ በተመለከተው አግባብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሀ/ ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት ለሚሰራ የትርፍ ሰዓት ስራ ለመደበኛ ስራ በሰዓት ከሚከፈለው ደመወዝ በአንድ ነጥብ  አምስት (1.5) ተባዝቶ፣

ለ/ ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት ለሚሰራ የትርፍ ሰዓት ስራ ለመደበኛ ስራ ሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በአንድ ነጥብ ሰባት አምስት (1.75) ተባዝቶ፣

ሐ/ በሳምንት የእረፍት ቀን የሚሰራ የትርፍ ሰዓት ስራ ከመደበኛ ስራው በሰአት የሚከፈለው ደመወዝ በሁለት (2) ተባዝቶ፣

መ/ በህዝብ በዓላት ቀን ለሚሰራ የትርፍ ሰዓት ስራ ለመደበኛ ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በሁለት ነጥብ አምስት (2.50) ተባዝቶ፣

4.4.2. የትርፍ ሰዓት ክፍያ ለደመወዝ መክፈያ በተወሰነው ቀን ከደመወዝ ጋር ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡

4.4.3. ማንኛውም የትርፍ ሰዓት ስራ ሊቆጠር የሚችለው አንድ ሰራተኛ በቀን ከ8፡00 ሰዓት በላይ በሳምንት ደግሞ ከ39፡00 ሰዓት በላይ ሰርቶ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

## 4.5. የትርፍ ሰዓት ስራ መጠን

ሀ/ ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቋሚ የስራ ቀናት ውስጥ በቀን 5 ሰዓት በወር ውስጥ ደግሞ ከ80 ሰዓት ያልበለጠ ትርፍ ሰዓት ሊሰራ ይችላል፡፡ ከዚህ በላይ መስራቱ የተረጋገጠ ሰራተኛ የሰራው ሰዓት ተሰልቶ የማካካሻ እረፍት ይሰጠዋል፡፡

ለ/ በሳምንቱ የእረፍት ቀናት ውስጥ በቀን ከ6 ሰዓት ላልበለጠ ሰአት ሊሰራ ይችላል፡፡ ከዚህ በላይ የሚያሰራ ከሆነ ደግሞ በፈረቃ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

ሐ/ በህዝብና በሐይማኖታዊ በአላት በቀን ከ6 ሰዓት ለማይበልጥ ሰዓት ሊሰራ ይችላል፡፡ ከዚህ ሰዓት በላይ የሚያሰራ ከሆነ በፈረቃ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

## 4.6 የትርፍ ሰዓት ስራ አፈቃቀድና የማረጋገጫ ሰዓት

ሀ/ የትርፍ ሰዓት ስራ አፈቃቀድ በተመለከተ በአንቀጽ 4.1 ለ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

ለ/ የስራ ክፍል ኃላፊዎች ባለሙያውን የሚሰራው ስራ ታውቆ፣ ለስራው የወሰደው ጊዜ ተመዝግቦ መሆን አለበት፣

ሐ/ በትርፍ ሰዓት ገብተው ለሚሰሩ ሰራተኞች ትርፍ ሰዓት ክፍያ በተቀመጠው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ቀመር መሠረት የሚከፈል ሲሆን ትክክለኛነቱን በዳይሬክተሩ ተረጋግጦና በዘርፉ ምክትል ስራ አስፈጻሚ ሲያፀድቅ ብቻ ክፍያ ይፈፀማል፡፡

መ/ በመደበኛ የእለት ስራው መሰራት ያለበትን ሳይሰራ ቀርቶ ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጪ የሚደረግ ስራ እንደትርፍ ሰዓት አይቆጠርም፡፡ ይህ አድርጎ መገኘት

ሠራተኛውንም ሆነ የፈቀደው የስራ ክፍል/ዘርፍ/ ኃላፊው በዲስፕሊን ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ሠ/ የሳምንቱ የእረፍት ቀን የትርፍ ሰዓትና የጉዞ አበል ክፍያ ተደርቦ ክፍያ አይፈፀምም፡፡

ረ/ ሠራተኛው በሥራ ላይ የቆየባቸው ጊዜያት ብቻ በትርፍ ሰዓት ስራ ይመዘገብለታል፡፡

ሰ/. ተቋሙ የትርፍ ሰዓት ስራ ቆይታ ለመመዝገብ በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ አሰራርን ሊከተል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 5
## የተሻሩ ድንጋጌዎች

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረው የትርፍ ስዓት ክፍያ በአዲሱ የትርፍ ስዓት ክፍያ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## አንቀጽ 6
## መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ የሰራተኞች የትርፍ ስዓት መመሪያ በተቋሙ ስራ አመራር ቦርድ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 7
## የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የትርፍ ስዓት መመሪያ በሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 8
## መመሪያው በስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ የትርፍ ስዓት ክፍያ መመሪያ ቁጥር 105 በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ስራ አመራር ቦርድ ከፀደቀ ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡